## ያግኙን

እርስዎ ወይም እርስዎ የሚያውቁት ሰው ከሥቃይ የተርፈ ድጋፍ፣ ፈውስ እና ማገገምን የሚፈልግ ከሆነ እኛ ለእርስዎ አለን! በሕይወትዎ ውስጥ ይህን አዲስ ምዕራፍ ሲጀምሩ ዐሳቢ እጅ እና ሩህሩህ ልብ  እናቀርብልዎታለን። አንድ ላይ ሆነን ወደፊት ብሩህ  ሕይወት መስራት እንችላለን።

## የመገኛ አድራሻ


ስልክ: 612-436-4855

ኢሜይል: SPHCintake@cvt.org

ድህረ ገጽ: www.cvt.org


# አድራሻችን



አድራሻ:

649  ዴይተን አቬኑ(Dayton Avenue)

ቅዱስ ጳውሎስ፣ ኤምኤን(St. Paul,

በአካል የምንገናኝባቸው ሰዓቶች ይለያያሉ መጀመሪያ መደወል ወይም ኢሜይል መላክ የተሻለ ነው

# ሲቪቲ - ቅዱስ ጳውሎስ የፈውስ ማዕከል

The CENTER for VICTIMS of TORTURE



# እኛ ማን ነን?

በSPHC፣ እኛ እርስዎን ለመደገፍ እዚህ የተገኘን የተንከባካቢ ባለሙያዎች ቡድን ነን። በዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ ጥገኝነት ጠያቂዎች የሚያጋጥሟቸውን ተግዳሮቶች እንረዳለን። ፈውስ እና የመቋቋም አቅምን ለማሳደግ ደንበኞቻችንን በአክብሮት እና በክብር ለማገልገል ቁርጠኞች ነን። የግለሰብ እና የቡድን አገልግሎቶችን ባለንበት ቦታ በቅዱስ ጳውሎስ እና በኦንላይን እናቀርባለን።

## ማንን ነው የምናገለግለው?

በቅዱስ ፖውሎስ የፈውስ ማዕከል፣ በቅርቡ ወደ ዩናይትድ ስቴትስ የገቡ ከማስቃይ የተረፉ ሰዎችን ለመደገፍ የተነደፉ አገልግሎቶችን እንሰጣለን። ብዙ ደንበኞቻችን በስደት የሚኖሩት ወይም በአሜሪካ ውስጥ ጥገኝነት ለማግኘት የሚጠይቁት በመንግስቶቻቸው ከተሳደዱ በኋላ ነው። ደንበኞቻችን በዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ ስላለው የማህበራዊ አገልግሎቶች መረጃ እና ጭንቀትን እና ጉዳቶችን እንዴት መቋቋም እንደሚችሉ መረጃ ይፈልጋሉ። ዘር፣ ቋንቋ፣ ጾታ፣ ዕድሜ፣ ሃይማኖት፣ወይም የኤል ጂ ቢ ቲ ኪው( LGBTQ) ሁኔታ ምንም ሳይለይ ማንኛውንም ሰው እናገለግላለን። እኛ እርስዎን ለመርዳት እዚህ ነን!

## ባህል እና ቋንቋ

ለደንበኞቻችን በባህልና በቋንቋ ተስማሚ የሆኑ አገልግሎቶችን እናቀርባለን። ሠራተኞቻችን ፈረንሳይኛ፣ ሶማሊኛ፣ ኦሮሞ፣ ስፓኒሽ እና አማርኛን ጨምሮ በርካታ ቋንቋዎችን ይናገራሉ። ቋንቋችሁን የማናውቅ(የማንረዳ) ከሆነ፣ ለመግባባት የሚረዳን አስተርጓሚ ባለሙያ እናገኛለን። አገልግሎቶቻችን ባህልዎን እንዲያከብሩ ከእርስዎ ጋር አብረን እንሠራለን።

## ከስቃይ የተረፉ ሰዎች ጋር ግንኙነት

የማህበረሰብ ፕሮግራሞቻችን ከሌሎች ከስቃይ የተረፉ ሰዎች ጋር ለመገናኘት እና ስለ ጤንነት እና ስለ ሌሎች ርዕሰ ጉዳዮች ለመማር ጥሩ መንገድ ናቸው። የማህበረሰብ ፕሮግራሞቻችን ከስቃይ የተርፉ ሰዎችን ማግኘት ( የአቻ ድጋፍ ቡድን) እና ሲቪቲ ዩናይትድ( የእግር ኳስ ክለብ) ን ያካትታሉ። ወቅታዊውን የጊዜ ሰሌዳ ወደ www.cvt.org/community የሚለውን ድረ-ገጽ

______ ______

## አገልግሎቶቻችን

### የሥነ ልቦና ህክምና(ሳይኮቴራፒ)

በዩናይትድ ስቴትስ በክሊኒካችን ውስጥ ከአስከፊ ስቃይ የተረፉ ሰዎችን እና የጥገኝነት ጠያቂዎችን ሊገጥሟቸው የሚችሉትን ተግዳሮቶች የሚረዱ ዐሳቢ ቴራፒስቶች(ሀኪሞች) ቡድን አለን። የህክምና ባለሙያዎቻችን እንደ እንቅልፍ ማጣት፣ ፍርሃት፣ የዕለት ተዕለት ጭንቀት እና ሌሎች ጉዳዮችን ለመፍታት ሊረዱዎት ይችላሉ። በአዲሱ ቤትዎ ውስጥ የተሻለ ስሜት እንዲሰማዎት እና ሰላም እንዲያገኙ በጉዞዎ ላይ እርስዎን ለመደገፍ እዚህ መጥተናል።

### የህክምና እርዳታ

የእኛ የህክምና ባለሙያዎች(ነርሶዎች) ስለህክምና ፍላጎቶችዎ ሊያነጋግርዎት እና በአካባቢዎ ዶክተር ወይም ክሊኒክ እንዲያገኙ ሊረዳዎት ይችላሉ። የማህበረሰብ ጤና ሰራተኞቻችን ጤናማ ህይወት መኖር እንዲችሉ እንደ አመጋገብ እና የአካል ብቃት እንቅስቃሴ ያሉ ርዕሰ ጉዳዮችን  እንዲማሩ ሊረዱዎት ይችላሉ።

### ማህበራዊ አገልግሎቶች

ከአዲስ ማህበረሰብ እና ባህል ጋር መላመድ ፈታኝ ሊሆን ይችላል። በዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ ካለው ህይወት ጋር እንዲላመዱ የእኛ ሰው ተንከባካቢ እና አክባሪ የጉዳይ አስተዳዳሪዎች እና የማህበረሰብ ጤና  ሰራተኞች እርሶዎን ለመርዳት እዚህ አሉ። እንደ እንግሊዝኛ የትምህርት ክፍሎች፣ የሥራ ማሰልጠኛ ፕሮግራሞች፣ የምግብ እና መጓጓዣ ላሉ ተግባራዊ ፍላጎቶች ግብዓቶችን እንዲያገኙ ሊረዱዎት ይችላሉ። እነዚህን ፍላጎቶች በማሟላት ደህንነቱ የተጠበቀ እና በራስ የመተማመን  ለወደፊት መሰረትን እንዲገነቡ እናበረታታዎታለን።